# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 68 ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም


> ነፃነት ሳይኖር ሰላም ፣ ሰላም ሳይኖር ደግሞ እድገት የለምና ነፃነት፤ ሰላምና እድገት የምትፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመንገዳገድ ላይ የሚገኘዉን የመለስ ዜናዊን ስርዐት ለመጣል ክንድህን አንሳ!
>
> **አቶ ኤፍሬም ማደቦ**

ግዜ

## ግንቦት 7 ባሳለፍነው ወር የተሳካ ስራ መስራቱን ገለጸ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ለአባሎቹ በላከው ወርሀዊ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ላይ እንዳመለከተው፣ የንቅናቄው ተለያዩ ዘርፎች በነሀሴ ወር ውስጥ ከፍተኛ ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል። ንቅናቄው ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር የሚያደርገው ውይይት ፍሬ በማፍራት ላይ እንደሚገኝ ሪፖርቱ ገልጾ፣ በዲፕሎማሲው ረገድም ከተለያዩ አገሮች ጋር ጠንካራ ወዳጅነት በመመስረት ላይ መሆኑን አመልክቷል።

በርካታ ኢትዮጵያውያንም ንቅናቄውን ለመቀላቀል በእየለቱ በኢሜል፣ በፖስታና በስልክ በመጠየቅ ላይ መሆናቸውን ያመለከተው ንቅናቄው፣ እነዚህን አባሎች በህቡእ በማደራጀት ከፍተኛ የሆነ ድርጅታዊ አቅም በመፍጠር ላይ እንደሚገኝም ተናግሯል።

ከፖሊስ ሰራዊትና ከወታደሮች የሚመጣው መልእክት ለማመን የሚያስቸግር ነው የሚለው የግንቦት 7 ህዝብ ግንኙነት በበኩሉ፣ ሰራዊቱ ከወያኔ ሰላዮች ራሱን በመከላከል በወያኔ ላይ የጀመረውን የውስጥ ትግል አጠናክሮ መግፋት እንዳለበትም ተናግሯል።

የግንቦት 7 ድምጽ በመከላከያ ውስጥ ያለውን የብሄር ተዋጽኦ በተመለከተና በፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ተቀጥረው ሲያገለግሉ ከነበሩ የወያኔ የፖሊስ አባላት ጋር ያደረጋቸው ቃለ ምልልሶች በወታደሩ ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃት እንደፈጠሩ ወታደሮችን ዋቢ አድርጎ የገለጸው የግንቦት7 ህዝብ ግንኙነት፣ ወታደሮቹ ተወሳሳይ መረጃዎችን ለንቅናቄው ለመስጠትም ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አድማጮቻችን በዚህ አጋጣሚ የግንቦት7 ድምጽ ከተለያዩ የፖሊስ እና የመከላከኬአ አባላት ጋር በመገናኘት የሚያዘጋጃቸውን ቃለምልልሶች በቅርቡ በተከታታይ እንደሚያሰማ ይገልጻል።

## የመፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሲዘጋጁ ደርሽባቸዋለሁ በተባሉት ተከሳሾች ላይ ድብደባ መፈጸሙን ራሳቸው ተከሳሾች ገለጹ

ተከሳሾቹ ከትናንት በስቲያ በዋለው ይስሙላ ፍርድ ቤት ላይ እንደተናገሩት ፣ አይናቸው በጨርቅ ተሸፍኖ ከምሽቱ ሁለት ሰአት በሁዋላ ወደ ማእከላዊ ምርመራ እየተወሰዱ ይደበደቡ እንደነበርና የራሳቸው ያልሆነውን ቃል የራሳቸው ቃል እንደሆነ አድርገው እንዲፈርሙ መጠየቃቸውን ተናግረዋል።

እስረኞቹ አሰቃቂ ድብደባ ይፈጸምባቸው እንደነበር መናገራቸው ያናደደው የወያኔ ቴሌቪዥንም ዜናውን በተለመደው አድርባይነቱ ሳያቀርበው ቀርቷል።

የእስረኞች አያያዝ ህግ አንድ እስረኛ ከምሽቱ 11 ሰአተ ተኩል በሁዋላ ከታሰረበት ክፍል አይወጣም እንደሚል የተናገሩት ምንጮቻችን፣ ከግንቦት7 ጋር ተያይዞ የታሰሩት እስረኞች ግን በሌሊት እየተጠሩ ይደበደቡ፣ ውሀ ይፈስባቸውና ይንገላቱ ነበር ብለዋል።

ፍርድ ቤቱ የይስሙላ ባይሆን ኖሮ እንዲህ ያደረገቱት ፖሊሶች ተጠርተው ይጠየቁ ነበር የሚሉት የህግ ባለሙያዎች በበኩላቸው፣ በማስገደድ የተገኘ መረጃ በመረጃነት ስለማይያዝ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ማድረግ ይጠበቅበታል ብለዋል።

ከአዲስ አበባ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው እስረኞቹ የሚደርስባቸውን ተጽኖ ተቋቁመው፣ የወያኔን ጭካኔ ባደባባይ ለማጋለጥ መወሰናቸው ህዝቡን በእጅጉ ያስደሰተ ሆኗል።

## ከአሜሪካ መንግስት ጋር በየጊዜው በመላተም ላይ የሚገኘው ወያኔ፣ ሰሞኑን ደግሞ የአሜሪካ መንግስትን በመንግሰት ግልበጣ ወንጀል መክሰሱ ብዙዎችን አስገረመ

ወያኔ በአዲስ ዘመን ላይ ጽፎ ባሰራጨው ጽሁፍ ላይ የአሜሪካ መንግስት አሁን ያለውን አገዛዝ በሀይል ለመጣል እየሰራ ነው ሲል ክስ አቀርቦ፣ የአሜሪካና የዩኤስ ኤአይዲ ባለስልጣናት ከዚህ ደርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው ሲልም አሳስቧል። ወያኔ በአሜሪካ ላይ ያቀረበው ክስ ዝርዝር ጉዳዮችን ያላስቀመጠ ቢሆንም፣ ሰሞኑን በዩኤስ ኤአይዲ ላይ የሰነዘረው ወቀሳ ከዚህ ክስ ጋር ተያይዞ የቀረበ መሆኑን ግን ለማወቅ ተችሏል። ወያኔ ለአሜሪካ የሰጠው ማስጠንቀቂያም "በማን ላይ ቆመሽ እግዜሄርን ታሚያለሽ" የሚሉትን የአበው አባባል የሚያስታውስ ሲሆን፣ የወያኔ ድፍረትና ትእቢትም ብዙዎችን እያስገረመ መምጣቱን የሚደርሱን አስተያየቶች ያመለክታሉ።

የአሜሪካ መንግስት የብረቱካንማ አብዮት ለማድረግ ሲጥሩ ከነበሩ ሀይሎች ጋር አብሮ በመስራት ላይ ነው የሚል ክስ ያቀረበው ወያኔ፣ የብረቱካን አብዮት ለማድረግ ይሰራሉ ያላቸውን ሀይሎችን ግን አሁንም ከመጥቀስ ተቆጥቧል። ይሁን እንጅ ከተለያዩ ምንጮች ባሰባሰብነው መረጃ መሰረት ወያኔ የአሜሪካ መንግስት ከግንቦት 7 ሀይሎች ጋር በጋራ እየሰራ ነው የሚል ክስ ማቅረቡን ለማወቅ ችለናል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## ወያኔ በተለመደ ማጭበርበሩ ፈረንጆችን ለማታለል ከተቃዋሚዎች ጋር እደራደራለሁ አለ

በምርጫ 97 ላይ ከፍተኛ ሽንፈት ገጥሞት የነበረው ወያኔ ለመጭው 2002 ምርጫ ተብዬ ድራማ ህጋዊነት ሊያስገኝለት የሚችል በአጃቢነት የሚሳተፍ ተቃዋሚ ለማግኘት ደፋ ቀና በማለት ላይ እንደሚገኝ በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር ከሚገኙ መገናኛ ብዙሃን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማወቅ ተችሎአል ።

በፓርላማ ተብዬው ውስጥ የሚገኙ አብዛኛው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይቀሩ ከወከላቸው ህዝብ ጋር እንዳይገናኙ ከፍተኛ አፈናና ወከባ እየተፍጸመብን ነው በማለት ከምንጊዜውም በላይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት ላይ በሚገኙበት በዚህን ሰዓት፣ የወያኔ ከተቃዋሚዎች ጋር ስለ መርጫ አካሄድ ለመወያየት መፍቀድ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ብቻ እንደሆነ እያወቀ ለመሞኘት ከተዘጋጁት ውጭ ሁሉም ይረደዋል ተብሎአል ። ይህ በዚህ አንዳለ ሰብ ሳህራን ኢንፎርመሽን የተባለ ጋዜጣ ባለፈው ሳምንት ህትመቱ ወያኔ ከሚያደርስባቸው ከባድ አፈና አንጻር የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች **ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## አባ ጳውሎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርሲያን ላይ እየፈጸሙ ያሉትን ጥፋት በመቃወም ሁለት የሀይማኖት አባቶች ኤርትራ ገቡ

የኤርትራ የኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር ባለፈው ሳምንት ይፋ እንዳደረገው የሀይማኖት አባቶቹ በልደታ ቤተክርሲቲያን ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩት መላከ ጸሀይ አባ ዮሀንስና የስላሴ ገዳም አገልጋይ የነበሩት ቄስ ጥበቡ አስፋው ናቸው።

የሀይማኖት አባቶቹ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሙስና፣ ዘረኝነት፣ ስርአት አልበኝነትና ስርቆት በከፍተኛ ደረጃ ተባብሷል። አባ ፓውሎስ ከወያኔ ጋር በማበር የሀይማኖት አባቶችን እንደሚያስገድሉ፣ ከስራ እንዲፈናቀሉና እንዲደበደቡ እንደሚያደርጉ የገለጹት አባቶቹ፣ ብዙ የሀይማኖት አባቶችም ነፍሳቸውን ለማቆየት የተለያዩ አማራጮችን በማፈላለግ ላይ ናቸው ብለዋል።

አባ ጳውሎስ በህወሀት የደህንነትና የጥበቃ ሰዎች ታጅበው እንደሚንቀሳቀሱ የገለጹት የሀይማኖት አባቶቹ፣ በዚህም ድርጊታቸው ጳጳሱ ራሳቸውን ከሃይማኖታዊ ሥራዎች አግልለዋል ብለዋል። አያይዘውም ከላይ እስከታች ድረስ የቤተክርሲያኒቱ ሀብት እየተዘረፈና ተጠያቂነት እየጠፋ ነው ብለዋል።

አባ ሳሙኤልን ከስልጣን ለማስነሳት አባ ጳውሎስ የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት የሀይማኖት አባቶቹ፣ እስካሁን ድረስ ግን በአንዳንድ የሲኖዶስ አባላት ተቃውሞ ምክንያት እንዳልተሳካላቸው ታውቋል።

አባ ጳውሎስ "ከአማሮች" ተጠንቀቁ እያሉ ይናገሩ እንደነበር የተናገሩት የሀይማኖት አባቶች፣ በአገሪቱ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ገዳማት የሚገኙ መነኮሳትንም ማስገደላቸውን አጋልጠዋል። **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## መምህራንና ት/ሚኒስቴር በወያኔና ቪ.ፒ.አር እየታመሱ ነው

የኢትዮጵያ መምህራን የወያኔና የተላላኪዎቹ ድርጅቶች አባል ካልሆናቸው ተብለው ወከባና እንግልት እንደሚደርስባቸው ከየአቅጣጫው የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። መምህር አንተነህ ቶሎሳ ከመቂ በኢሜል በላኩሉን መረጃ መሠረት በፓርቲ ስብሰባ አልተገኘህም ተብለው የ15 ቀናት ደመወዛቸውን ተቀጥተዋል። በተያያዘ ዜናም ቪ.ፒ.አር የተባለውን ተቃዋሚዎችን የማስወገጃ ስልት በመጠቀም የት/ሚኒስቴር የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች እየታመሱ ነው ተባለ። በቪ.ፒ.አር ሰበብ ለበርካታ ዓመታት በሚኒስትሩ መ/ቤት ያገለገሉ ነባር ሠራተኞች ሳይቀሩ ተባረው በምትካቸው ስለ ትምህርት አንዳችም ግንዛቤ የሌላቸው የመንደር ካድሬዎች የትምህርት አስተዳደርን ሥራ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው። ወ/ሮ አሰለፈች በድሉ በቪ.ፒ.አር ሰበብ ለ18 ዓመታት ያገለገሉትን የት/ሚኒስትርን የተሰናበቱት በእንባ ነበር:: «ከት/ሚኒስቴር የሚለየኝ ሞት ብቻ ነው ብዬ አስብ ነበር፤ ይኸው ወያኔ ከሞትም የከፋ ባላጋራ ሆኖ ከምወደው ሥራዬ ነጠለኝ» ሲሉ አስተያታቸውን ለግንቦት 7 ዘጋቢ ሰተተዋል፡

# የወያኔን የመረጃ አፈና ለመበጣጠስ በአንድነት እንነሳ

የመልካም አስተዳደር አንዱ ገጽታ ግልጽነት ነው። ግልጽነት ለተጠያቂነት በር ይከፍታል። ግልጽነት ካለ ዜጎች የመንግሥትን የእለት ተእለት ተግባር በቅርበት ስለሚከታተሉ ስህተቶች በወቅቱ ይታረማሉ። ለግልጽነት ደግሞ ነፃ እና ተዓማኒን መረጃ ማግኘትና መስጠት ቁልፍ ጉዳይ ነው። መረጃን አፍኖ ይዞ ስለ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት ከዚያም አልፎ ስለመልካም አስተዳደር መናገር ከንቱ ነው። በያዝነው ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መረጃ የሃብቶች ሁሉ ቁንጮ ሆኗል። መረጃን ማፈን እና ማዛባት ልማትን፣ ትምህርትን፣ ጤናን፣ ንግድን ባጠቃላይ የዜጎችን የእለት ተእለት ሕይወትን በእጅጉ የሚጎዳ ተግባር ሆኗል።

አምባገነኖች ግልጽነትን አጥብቀው ይጠላሉ። ወያኔ ደግሞ እስካሁን ካየናቸው አምባገኖች ሁሉ በባሰ የግልጽነት ጠላት ነው። ወያኔ መረጃን የመቆጣጠርና የማዛባት የማይረካ ጥማቱ ኢትዮጵያን በመረጃ ስርጭት ወደኋላ ጎትቶ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ይልቅ ጥንታዊና ባህላዊ የመረጃ ልውውጥ ስልቶች ይበልጥ ተዓማኒን እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይህንን በእለት ተእለት ሕይወታችን የምናየው ነገር ስለመሆኑ የሚከተሉትን ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል።

1. በአሁኑ ሰዓት ወገኖቻችንን እያጠቃ ያለው "**አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት (አተት)**" በሚል መጠሪያ ስለሚታወቀው በሽታ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰማው በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን ከተላለፉ ዜናዎች ሳይሆን በተለመደው ከሰው ወደ ሰው በሚዛመት ወሬ ነው። በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጉትጎታ እና ብዙ ሕዝብ ከተጎዳ በኋላ የወያኔ ሹማምንት የችግሩን ጫፍ ጫፍ ቢያነሱትም ስለበሽታው መከላከያ ዘዴዎች እና ህሙማኑን እንዴት መርዳት እንደሚገባ ከማስተማር ይልቅ "በሽታውን ተቆጣጥረነዋል፤ ወደ ገጠር እየተስፋፋ ነው የሚባለው አሉባልታ ነው" ለሚሉና የመሳሰሉ የመረጃ ማዛባት ዘመቻ ነው ትኩረት የሰጡት። መረጃ ማፈንና ማዛባት ምን ያህል ተጨባጭ ጉዳት እንዳለው አተት ከስሙ ጀምሮ ማስረጃ ነው። ይህ በሽታ በኢትዮጵያ ምድር ሲመላለስ አስርት ዓመታት ያሳለፈ ቢሆንም እስካሁን ስም አልወጣለትም ብሎ መዋሸት ምን ይባላል? አሁንም የዚህ በሽታ ምንነት፣ ባህርይና ስርጭት በሚስጢር በመያዙ ጉዳታችን ምን ያህል እንደሆነ አይታወቅም። ይህ በሽታ ከድህነት ጋር ስላለው ግኑኝነትም የተነሳ ነገር የለም። ምሳ መብላት ብርቅ እየሆነ ባለበት ሁኔታ ኮሌራን "አተት ትሰኛለህ" ቢሉት ለታማሚው ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም።
2. የወያኔ ቁንጮዎች መረጃ ሲነፍጉ፣ ሲዋሹና ሲቀጥፉ ለከት የላቸውም። በሶማሊያ ስለሞተው ጦራችን ብዛት "ፓርላማ" ብለው በሚጠሩት የአሻንጉሊቶች ሸንጎ በተጠየቀበት ወቅት መለስ "ፓርላማው ይኸንን ማወቅ አያስፈልገውም" በማለት በአሻንጉሊቶቹ አስመስሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ማወቅ እንዳለበት፤ ምን ደግሞ ማወቅ እንደሌለበት የሚወስነው እርሱ ብቻ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል። ስታሊን እንኳን እንዲህ በድፍረት ተናግሮ አያውቅም። በሌላ ጊዜ "ጠግበው ያልበሉ ህፃናት እንጂ ረሃብተኞች የሉንም" ዓይነት ለመረዳት የሚያስቸግር አባባል የተናገረውንም እዚህ ላይ እናስታውሳለን። ለወያኔ ሹሞች መረጃ የፕሮፖጋንዳ መሣሪያ እንጂ ከሃቅ ጋር አንዳችም ዝምድና ያላት ነገር አይደለችም። በዚህም ምክንያት ቁጥሮችና መቶኛዎችን እንደፈለጋቸው ይቀያይሯቸዋል። ለምሳሌ ስለ እድገት እያወሩ ከሆነ የረሃብተኞችን ቁጥር ዝቅ፤ የእርዳታ ልመና እያቀረቡ ከሆነ ደግሞ ከፍ አድርጎ ማቅረብ ወያኔን ደጋግሞ ትዝብት ውስጥ የጣለ ነገር ነው።
3. የአገሪቱ የእስታትስቲክስ መረጃዎች ፈረንጆች እንኳን ሳይቀሩ ‹‹እጅ እጅ ይላሉ›› እያሉ የሚያጣጥሏቸው ወቅት ላይ ደርሰናል። የአገሪቱ ማእከላዊ የእስታትስክስ ጽ/ቤት ስለምርትና ምርታማነት ቀርቶ ብዛታችንን እንኳን በትክክል ቆጥሮ ሊነግረን ያልቻለ፤ ለቁራጭ መረጃ እንኳን ተዓማኒነት ያጣ መ/ቤት ነው። የእስታትስቲክስ ጽ/ቤት ከገበያ የተሸመተ የእህል ክምር ተደግፎ ቪዲዮ እየተነሳ "እንዲህ ዓይነት ማዳበሪያና እንዲህ ዓይነቱን ዘር ተጠቅሜ ከግማሽ ሄክታር ማሳ ይኸንን ያህል አመረትኩ" እያለ ለጥቂት ባውንዶች ሲል ለኢትዮጵያ ቴሊቪዥን ከሚተውን የመንደር ተዋናይ የተሻለ ግምት መስጠት አለመቻሉ እየታየ ነው። ይሁን እንጂ የመረጃን ምንነት የሚያውቁ፤ ለራሳቸውም ለሙያውም ክብር ያላቸው ዜጎች በጽ/ቤቱ ውስጥ መኖራቸው ስለምናውቅ በሌሎች አገሮች እንደታየው ሁሉ እኛም አገር ባለሙያዎች ‹‹መረጃ መቀቀል ሰለቸን›› ብለው በግልጽ እንደሚያምፁ እንጠብቃለን። እስከዚው ግን የጽ/ቤቱ ሥራ እያጋለጡ የነገሮችን እውነተኛ ስእል በሚስጢር ማውጣት መቀጠል ይኖርባቸዋል።
4. በምሥራቅ ኢትዮጵያ ገጠሮች ውስጥ ህፃናትን በማስተማር የነፃ በጎ አድራጎት ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትና በወያኔ ሹማምንት ውሳኔ ተንገላተው በአስቸኳይ ከአገር እንዲወጡ ከተደረጉ አሜሪካዊያን ተማሪዎች አንዷ "የኢትዮጵዊያንን የእለት ለእለት የመከራ ሕይወት በትንሹ ቀመስኩ" ስትል በአገሯ ጋዜጣ የሰጠችው የምስክርነት ቃል ወያኔ በመረጃና ትምህርት ላይ ስላለው አቋም እንደ አንድ የቅርብ ጊዜ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል። የበጎ ፈቃድ መምህራኑ ከተወነጀሉባቸው ጉዳዮች አንዱ ተማሪዎችን "ከመጠን በላይ ማሳወቅ" የሚል እንደነበር ወጣቷ በአግራሞት ገልፃለች። የምሥራቅ ኢትዮጵያ ህፃናት ስለምን እምን ድረስ ማወቅ እንደሚፈቀድላቸው በዝርዝር የተገለፀ ነገር ባይኖርም "አብዝቶ" ማስተማር ግን ወንጀል ነው ተብሏል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ደግሞ በደቡብ ክልል ይቀሳቀሱ ለነበሩ አርባ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፈቃድ መሰረዝ የተጠቀሰው ምክንያት ከመንግሥት ፓሊሲ ጋር የማይጣጣም ነገር ገበሬዎችን አስተምረዋል፣ ቀስቅሰዋል የሚል እንደነበር በወቅቱ መዘገባች ይታወሳል።
5. ወያኔዎች መረጃን ማፈን፣ ማዛባትና የሚፈልጉትን መረጃ መፈብረክ የንግዳቸው አንዱ መሠረት አድርገውታል። የጉምሪክ ታሪፍ ለውጥን ታሳቢ ያደረገ ሸቀጥ ለውጡ ተፈርሞ በሚጸድቅበት እለት እቃው ጂቡቲ ወደብ ይደርሳል። የመብራት መቋረጥ እንደሚኖር አስቀድሞ የተነገራቸው ነጋዴዎች ጄኔሬተር በጊዜ አስገብተው መብራት ኃይል እራሱ በሚያደርግላቸው የማስታወቂያ እገዛ ትርፋቸውን ይዝቃሉ። የሲሚንቶ ገበያ ብዙ የተባለለት ስለሆነ እዚህ ላይ ማንሳትም አያስፈልግም። የመሬት እደላና የባንክ ብድሮችም እንደዚሁ። የወያኔ ጨረታዎች ጉዳይ ጣልያን ውስጥም ፓርላማ ውስጥ አከራክሯል። ይኸ ሁሉ እየሆነም መረጃ የታፈነበትን ኢኮኖሚ ‹‹የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ›› ብለው ሲጠሩት አፋቸው አይደናቀፍም።
6. በመጨረሻም ወያኔ ሕዝብ ነፃ መረጃ ያገኝባቸዋል የሚላቸውን መስመሮች ሁሉ ለመዝጋት የሚያደርገውን ጥረት የወያኔ ፀረ-መረጃነት አንዱ ማሳያ ነው። ነፃ ጋዜጦችንና ሬድዮችን ከለከለ። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠራቸውንም ቢሆን ስለማያምናቸው ዘወትር በግምገማ እየታመሱ ነው። ከውጭ አገር የሚተላለፉ የሬድዮ ሞገዶችን ለመረበሽ ለብዙ ሚሊዮን ወገኖቻችን ምግብ፣ ልብስና መድሃኒት መዋል ይችል የነበረውን ሃብት ያባክናል። የኢንተርኔት ድረገፆችን በመዝጋት አገራችን በመረጃ ድርቅ እንድትማስን ፈርዶባታል።

ለዚህ መፍትሄው ምንድነው? ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሚያደርጋቸው ዘርፈ ብዙ ትግሎች አንዱ በመረጃ አቅርቦት ዘርፍ እያደረገ ያለው ትንንቅ ነው። እያንዳንዱ ራሱን የሚያከብር እና አገሩን የሚወድ ዜጋ ያገኘውን መረጃ በፍጥነት ለግንቦት 7 በማድረስ የወያኔን የመረጃ አፈና ካሁኑ መበጣጠስ እንችላለን። ይህ ደግሞ በሌሎች ዘርፎች ከሚደረገው ትግል ጋር ተቀናጅቶ ወያኔን የምንገላገልበትን ጊዜ ያፈጥንልናል።

ስለሆነም በወያኔ እስር ቤቶች የሚገኙ ወገኖቻችን ስላሉበት ሁኔታ፤ የወያኔን ተንኮሎች፣ እቅዶች፣ ስልቶች፤ ሕዝባችን ስለሚደርስበት ሰቆቃ ተጨባጭ መረጃዎች እንዲደርሱን ማድረግ ትግሉን የመቀላቀያ አንድ መድረክ መሆኑን ተረድታችሁ ተባብረን የወያኔን የመረጃ አፈና እንበጣጥስ። በማናቸውም የሥራ መደብ ላይ ቢሆኑ በእጅዎ የገባቸውን ትንሽ የምትመስለዋን እንኳን መረጃ ያለ አንዳች ማጋነንም ሆነ መቀነስ በ info@ginbot7.org ይላኩልን። የወያኔን የመረጃ አፈና ብቻ ሳይሆን ራሱ ወያኔን በአጭር ጊዜ ውስጥ እናስወግዳለን።

## ወያኔ በተለመደ ማጭበርበሩ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በመጪው ምርጫ መሳተፋታቸው አጠራጣሪ አንደሆነ ዘግቦአል ። የዜና ምንጬ ወያኔ አካሂዳለው ለሚለው ቀጣዩ የይስሙላ ምርጫ የእጩ ምዝገባ በሚቀጥለው ህዳር 2002 አመተ ምህርት የሚጠናቀቅ ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ ተቃዋሚዎች ይህ ነው የሚባል ዝግጅት ለማድረግ አልቻልንም በማለት ፓርቲዎች ያቀረቡትን ስሞታ በማጥቀስ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል ። ወያኔ ምርጫን አስመልክቶ ከሚታወቅበት የማጭበርበርና የማፈን ስልቱ በተጨማሪ በተዘረፈ የህዝብ ድምጽ የተቋቋመው ፓርላማ ያጸደቀው አዲሱ የምርጫ ህግ ተቋዋሚዎች ነጻ ምርጫ ይደረጋል ብለው እንዳያስቡ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗቸዋልም ተብሎአል።

ጋዜጣው የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ አመራር አባል ተመስገን ዘውዴ «አንድነት የቱንም ያህል ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲካሄድ ቢፈልግም አዲሱ የምርጫ ህግ እና የወያኔ ጉዳይ ፈጻሚ የሆኑት ተቋማት እስካሉ ነጻ ምርጫ አዳጋች መሆኑን መናገራቸውንና "ገዢው ፓርቲ ሆን ብሎ ይዞት የመጣው አዲስ ህግ በዴሞክራሲያው ምርጫ የመሳተፍ መብታችንን የሚገድብ ነው" ማለታቸውን ዘግቦአል ። አቶ ተመስገን ባቀረቡት ስሞታ መሰረት አንድነት ቢሮዎች እንዳይከፍት መታገዱንና አባላቶቹ በተለያዩ ቦታዎች በእስር እና በእንግልት እየተሰቃዩ መሆናቸውም ተገልጾአል።

ይቀጥላል ⟶

በተመሳሳይ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በምጽሀሩ አፍዴን ሊቀመንበር አቶ ብልቻ ደመቅሳ በወያኔ ምርጫ መሳተፍ ምንም እርባና እንደሌለው ተናግረዋል።

"እንዴት ከህዝባችን ጋር መቀራረብ እና መነጋገር ሳንችል ስለምርጫ ዝግጅት ልናስብ እንችላለን?" ያሉት አቶ ብልቻ አባላላቶቻቸው ከአዲስ አበባ ውጪ ወደ የትም መንቀሳቀስ እንዳማይፈቀድላቸውና ቢሮ መክፈትም መከልከላቸውን በምሬት ያስረዳሉ።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ደጋግሞ ለህዝብ ይፋ እንዳደረገው ነጻ ምርጫ ለማካሄድና የመራጬን ህዝብ ውሳኔ ለማስከበር የሚያስችል ተቋም በሌለበት ለወያኔ የይስሙላ ምርጫ አጃቢነት መሰለፍ አገራችንን ከወያኔ ጥፋት ህዝባችንም ከሰቆቃ ለማላቀቅ ለሚደረገው የምር ትግል ምንም ፋይዳ አንደማይኖረው መግለጹ ይታወሳል ።

የዝግጅት ክፍላችን ለአገራቸውና ለህዝባቸው ለሚቆረቆሩ አውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አና ደጋፊዎቻቸው ወያኔ በድህሬ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመውን ዓይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ከአሁን ቦኋላ አንዳይደገም ህዝባችንን በባዶ ተስፋ ስለ ምርጫ ከመቀስቀስ አንዲቆጠቡ፣ በምትኩ ዘረኝነትና አድሎአዊነት በአስቸኳይ ተገርስ'ሶ አንዲወድቅ የተጀመረውን ሁለገብ ትግል ለማፏፏም እንከተለዋለን በሚሉት ሰላማዊ የትግል ስትራቴጂ ተግተው እንዲፋለሙ ጥሪውን ያስተላልፋል ።

## ሃይለ ሀሳብ

# ወገን በረሀብ ሲጎዳ የጓዳዉን ለባዳ !!

ከኤፍሬም ማደቦ

የረጅሙን ዘመን ታሪካችንን ትተን ያለፈዉን 150 አመት ታሪካችንን ብቻ መለስ ብለን ብንመለከት የኢትዮጵያ ህዝብ ከዉጭ ወራሪዎች ወይም ከአገር ዉስጥ ጨቋኞች ተገላግሎ በሠላማዊ የእድገት ጎዳና የተጓዘበት ወቅት ወይም አጋጣሚ የለም። እንድ በጣም የሚያሳዝን ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ የዉጭ ጠላቶቹን አሸንፎ አንፃራዊ ሠላም አግኝቶ በኖረበት ዘመንም ቢሆን ከገዢ መደቦች እርግጫና ብዝበዛ እንዲሁም ከረሀብና ከሥራ አጥነት ተገላግሎ እፎይ ብሎ ኖሮ ለጡረታ የበቃበት አንድም ግዜ የለም።

የአገራችንን ህዝብ ታሪክ በሚገባ ላስተዋለዉ - የኢትዮጵያ ህዝብ ከዉጭ ጠላቶቹ ጋር ግብግብ ገጥሞ ጠላቶቹን አሸንፎና ዳር ድንበሩን አስከብሮ ሲመለስ የአገር ዉስጥ ጠላቶቹ ይረከቡቱና የተዋጋለትና የተዋደቀለት አገር የሱ እስካይመስለዉ ድረስ ያሰቃዩታል። ባለፉት 50 ዐመታት ዉስጥ ይህን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚደርሰዉን በደል በሚገባ የተገነዘበ 3 ትዉልድ በየተራ እየተነሳ በኢትዮጵያ ዉስጥ ህዝባዊ አስተዳደር ለመመስረት ታግሏል። ሆኖም ይህ አንዳንዴ በተጠና መልኩ በአብዛኛዉ ግን በግብታዊነት የተተካሄደዉ ትግል መስመር የያዘ ለዉጥ አምጥቶ የህዘብን የለዉጥ ጥማት ያረካበት ግዜ የለም።

በኢትዮጵያ ህዝብ የመብትና የነፃነት ትግል ዉስጥ በፋና ወጊነታቸዉ ምን ግዜም ሲታወሱ ከሚኖሩ የትግል እንቅስቃሴዎች ዉስጥ አንዱ በመሬት ላራሹ ዙሪያ የተሰባሰበዉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ነዉ። ይህ ስመ ጥሩ እንቅስቃሴ ብዙ አገራቸዉን የሚወዱ አርቆ አስተዋዮችን እንደፈጠረ ሁሉ ዛሬ የኢትዮጵያን ገበሬ "የመሬት ያለህ" ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ለሙን የአገራችንን መሬት ለባዕዳን በገፍ የሚቸበችበዉን ዘረኛዉን የወያኔ ቡድንም ፈጥሯል። የተነሱበትን ህዝባዊ አላማ እንደ መጠሪያ ስማቸዉ የሚቀያይሩት የወያኔ መሪዎች በተማሪነት ግዜያቸዉ ያነገቡትን የመሬት ላራሹ ጥያቄ አርግፍ አድርገዉ ትተዉ ዛሬ አገራችን አይታዉ የማታዉቀዉ የጭካኔና የዘረኝነት ምልክት ሆነዋል።

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት ሁኔታ በረጂሙ ታሪካችን ዉስጥ በዬትኛዉም ወቅት አጋጥሞን የማያዉቅ እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ ሁኔታ ነዉ። በኤኮኖሚ አድገናል ተብሎ መንገድና ህንፃ በተሠራ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ ድህነት እንደመንገዱ እየረዘመና እንደ ህንፃዉ እየሰፋ ይሄዳል። በአንድ በኩል የጎሳዉ ፌዴሬሺን የብሄር ብሄረሰቦችን ችግር አስወግዶ እኩልነትን ፈጥሯል ይባላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሚያዘዉ ፤የሚሾመዉና የሚሸረዉ በአጠቃላይ አገሪቱን ወዳሰኘዉ አቅጣጫ የሚነዳት የአንድ ብሄረሰብ ዉጤት የሆነ የዘረኞች ስብስብ ነዉ።

የኢትዮጵያን ህዝብ እንዲቀልብ አደራ ለተጣለበት ለኢትዮጵያ ገበሬ ነጥብ 93 ሄክታር መሬት በዛበት እየተባለ ለም መሬታችንን አርሰዉ የራሰቸዉን ህዝብ ለሚቀልቡ ባዕዳን ግን ከ3ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ተከልሎላቸዋል። ይህ መረን የለቀቀ የመሬት ንግድ የሚያሳያን ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዉያን ጥቅም ቅንጣት ያክል ደንታ የሌለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የባህር ማዶ የባንክ ሂሳቡ እስከደለበለት ድረስ የማይሸጠዉና የማይለዉጠዉ ምንም ነገር እንደሌለ ነዉ።

ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ በዉጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ ብዙ አምራች ድርጅቶች ሠራተኛ አባርረዉ በራቸዉን እየዘጉ ነዉ።የኢትዮጵያ ህዝብ- እንግዲህ ይታይህ! እንደዚህ አይነት ብሔራዊ ችግር ባለበት አገር ዉስጥ ነዉ ወያኔ የአገሪቱ የዉጭ ምንዛሪ ምንጭ የሆነዉን የሰሊጥ ምርት ኢትዮጵያ ዉስጥ አምርተዉ ወደ አገራቸዉ እንዲልኩ ለቻይና ካምፓኒዎች መሬት በገፍ የሚቸበችበዉ። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ በሰሊጥ ምርት የሚተዳደረዉ የጎንደር ህዝብ እንዲያዉቀዉ የምንፈልገዉ ነገር አለ፤ ቻይና አብዛኛዉን የኢትዮጵያ የሰሊጥ ምርት የምትገዛ አገር ናት፤ እንግዲህ ቻይና ኢትዮጵያ ዉስጥ መሬት ገዝታ ሰሊጥ እያመረተች ወደ ቻይና ላከች ማለት በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ከሰሊጥ የምታገኘዉ የዉጭ ምንዛሪ ቀረ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሰሊጥ ምርት የሚተዳደረዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሥራ አጥነት ተዳረገ ማለት ነዉ። ይህ ነዉ እንግዲህ ወያኔ ስራ አጥነትንና የዉጭ ምንዛሪ እጥረትን ለማስወገድ የቀየሰዉ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" የሚሉት የኤኮኖሚ ፖለሲ!

በወያኔ የመሬት ሽያጭ ዘመቻ ላይ የተሰማሩት ህንድ፤ ቻይናና ሳዑዲን የመሳሰሉ አገሮች መልሰዉ መላልሰዉ እንደተናገሩት ከሆነ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚያመርቱትን ምንም አይነት ምርት በቀጥታ ወደ አገራቸዉ ነዉ የሚወስዱት፤ የወያኔ ባለስልጣኖች ግን የመሬቱ ሽያጭ ዋና አላማ ኢትዮጵያን ከምግብ ጥገኝነት ለማላቀቅ ነዉ እያሉ ለዚህ አሳፋሪ ድርጊታቸዉ ህጋዊ ሽፋን ለመስጠት ይሞክራሉ። ቻይና፤ ሳዑዲና ህንድ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምግብ አምርተዉ የራሳቸዉን ህዝብ በቀለቡ ኢትዮጵያ እንዴት ከምግብ ጥገኝነት እንደምትላቀቅ ግልፅ የሆነ ነገር ባይኖርም፤ በዚህ ሐላፊነት በጎደለዉ የመሬት ሽያጭ ወያኔና "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ባይ አጨብጫቢዎቹ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚዎች መሆናቸዉ ግን ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልፅ ይመስለናል።

የኢትዮጵያ ህዘብ ሆይ ዘመን በዘመን በተተካ ቁጥር ከዛሬ ነገ ያልፍልኛል እያልክ ዛሬን በነገ እየለወጥክ ኖረሃል፤ ሆኖም ባለፉት 40 ዐመታት በግልፅ እንደታየዉ ዘመን በተለወጠ ቁጥር የሚያልፍላቸዉና የምድር ላይ ገነታቸዉን የሚቀጩት ስማቸዉን እየለዋወጡ የሚመጡብህ የገዢ መደቦች ብቻ ናቸዉ፤ ለዚህ ነዉ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ትልቁ ትግል ህዘብን ከችግርና ከድህነት ነፃ ለማዉጣት ሳይሆን ሥልጣን እንደያዙ ለመቆየት የሆነዉ።

ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት ታገልን የሚሉ ከሀዲዎች አዲስ አበባ ዉስጥ ባንተ ገንዘብ ቪላ እየገነቡ አዘቦቱን ሠርግና ምላሽ እሁድና ቅዳሜን ደግሞ ፋሲካ አድርገዉታል፤ አንተ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ዐመት ጠብቀህ ለምታከብረዉ ፋሲካ- እንኳን ዶሮ ሽንኩርት መግዛት አቅቶሀል። ልጅ ወልደህ እንዳታሳድግ እንኳን ለወለድከዉ ልጅ ለራስህ የምትበላዉ የለህም፤ ብቻህን እንዳትኖር ደግሞ የሚጦርህ አይኖርም።ካቻምና በሁለት በሬ አምና በመቀናጀ ታርስ ነበር፤ ዘንድሮ በሬዉም ማረሻዉም ተሸጦ ላልተጠቀምክበት ማዳበሪያ ዕዳ ከፋይ ሆነሃል፤ ከኤኮኖሚዉ ችግር የተነሳ አንተ በሁለት ቀን አንዴ - ልጆችህ ደግሞ በፈረቃ ሆኗል የምትበሉት። ይጦሩኛል ብለህ ተቸግረህ በዕዳ ያሳስተማርካቸዉ ልጆችህ "እራሳችሁን" የወያኔ ሎሌ ካላደረጋችሁ ስራ አትቀጠሩም ተብለዉ እቤት መዋል ከጀመሩ ቋይቷል። ይሄ ሁሉ አይችሉት ዕዳ ተጨኖብህ ከወደቅክበት ሳትነሳ አመት ይደርስና ግብር ሰብሳቢዉ መጥቶ የቀረህን ሁሉ አሟጦ ባዶህን ጥሎህ ይሄዳል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የገበያ አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም በፈጠረዉ ችግር የተነሳ የዋጋ ንረት በየቀኑ እየጨመረ ይሄዳል፤ ሰኞ በ6ብር የተገዛ አንድ ኪሎ ጨዉ ሐሙስ በ10 ብር ተፈልጎ አይገኝም፤ ከዚህ ሌላ የወያኔን ካምፓኒዎች ለመደጎም ከመንግስት ካዝና የሚወጣዉ ወጪ፤ የነአዜብ መስፍንንና የነ ስብሐት ነጋን አይን ያወጣ ዝርፍያ ለመሸፈን ከአንዱ የመንግስት ባንክ ወደ ሌላዉ የመንግስት ባንክ የሚንከባለለዉ የተቆለለ ዕዳና ከቁጥጥር ወጭ የሆነዉ የገንዘብ አቅርቦት እድገት ይህ ነዉ የማይባል ችግር እየፈጠረ ነዉ። ይህ ችግር ሸማቹ ከተሜ የወር ገቢዉን ለምግብ ግዥ ብቻ እንዲያዉለዉ አርሶ አደሩን ደግሞ ለዘር ያስቀመጠዉን እንዲበላ አስድዶታል።

ሰፊና ለምለም አገር ይዞ፤ የረጂም ግዜ ታሪክና የራሱ የሆነ ፊደል ኖሮት መሪዎቹ መጠን የለሽ ኃብታሞች ሆነዉ እሱ ግን በድህነት የሚሰቃይ ህዝብ ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነዉ። ድህነት ደግሞ ፈጣሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያዘዘዉ የ40 ቀን ዕጣ ሳይሆን ስግብግብ መሪዎቹ የተዉለት መጠፎ ቅርስ ነዉ።የወያኔና የሆዳም ሎሌዎቹ ችግር ዉፍርትና ቁንጣን ሲሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ግን ከሦስቱ የቀን ፍጆታዎች እንዱን አገኝ ይሆን የሚለዉ ፍርሀት ነዉ።ዘረኞቹ የወያኔ ባለ ሥልጣኖችና ቤተሰቦቻቸዉ ከህዝብ የዘረፉትን ገንዘብ በከፍተኛ የዉጭ ምንዛሪ መንዝረዉ አዉሮፓና አሜሪካ ዉስጥ እያከማቹ ለነገዉ ኑሯቸዉ ዋስትና ሲገዙ ገንዘቡን የተዘረፈዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ነገ ምን እሆናለሁ በሚል የማያስተኛ ህልም እየባነነ ይኖራል።

ከደርግ የማይሻል ምንም ነገር የለም በሚል እምነት ብቻ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን ለ18 ዐመታት ተሸክሞታል። 18 ዐመት ደግሞ በዬትኛዉም መለኪያ ቢለካ ትንሽ ግዜ አይደለም። ዛሬ የወያኔን ዘረኝነት አንቀበልም ብለዉ እስር ቤቱን የሞሉትና አለዕዳቸዉ ሶማሊያ እየተላኩ በከንቱ የሚያልቁት የኢትዮጵያ ወጣቶች ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ ወይም ከመግባቱ ከሁለትና ከሦስት ዐመታት በፊት የተወለዱ ናቸዉ። ትዕግስት ከኢትዮጵያ ህዝብ የተፈጥሮ ባህሪዮች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ነዉ፤ ሆኖም የታገስናቸዉ ኃይሎች ካለ ርህራሄ ሲረግጡንና ሥጋችንን ጨርሰዉ አጥንታችንን እየጋጡ በዘረኝነት አለንጋ ሲገርፉን ትዕግስታችን አልቆ አትንኩን ባይነታችን በቁጣና በምሬት መገለፅ አለበት።

ወያኔ በ1987 እና በ1992 ዓም በተካሄደዉ ትርጉም የለሽ ምርጫ ከራሱ ጋር ተወዳድሮ አሸንፏል።በ1997ቱ ምርጫ አዲስ አበባ ዉስጥ በዝረራ መሸነፉን ሲረዳ የጫካ ዉስጥ ጠባዩ ተቀስቅሶበት በየክልሉ እየዞረ እያንዳንዱን የምርጫ ጣቢያ በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ ምርጫዉን ማሸነፉን ተናግሯል።ባለፉት 5 አመታት ደግሞ ወያኔ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን "ተቃዋሚ" የሚባለዉን ቃል እራሱን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት የሚቻለዉን ነገር ሁሉ አድርጓል።

የወያኔዉ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በፃፈዉ መጽሐፍ ዉስጥ- "በታዳጊ አገሮች ዉስጥ የዕድገት ፖሊሲ ተከታታይነት እንዲኖረዉ ፖሊሲዉን የነደፈዉ ገዢ ፓርቲ ለረጅም ግዜ በሥልጣን ላይ መቆየት አለበት" ብሎ ለራሱ ሥልጣን መራዘም ፋይዳ ቢስ ምክንያት ደርድሯል። የዛሬ ሁለት አመት በነፃነት ሀሳብን መግለጽ የሚከለክል ወይም ፕሬስን የሚያፍን የሜድያ ህግ አፅድቆ በስራ ላይ አዉሏል።በቅርቡ ደግሞ ማንንም ሰዉ እንዳሰኘዉ ማሰርና ማሰቃየት የሚያስችላቸዉን የሽብርተኝነት ህግ አርቅቆ አፅድቋል።

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እንደዚህ አይነቱን ምርጫንና ዲሞክራሲን የሚገድብና ተቃዋሚ ድርጅቶችን የሚያንቅ መሠናክል በየቦታዉ ገንብቶ የ2002ቱን ምርጫ ዉጤት ከወዲሁ ካረጋገጠ በኋላ ሰሞኑን በእርዳታ ለጋሽ አገሮች ግፊት ከ"ተቃዋሚ ድርጅቶች" ጋር መወያየት 'እንፈልጋለን' የሚል አዲስ ዘፈን መዝፈን ጀምሯል። ግፊቱና ጫናዉ ከአዉሮፓም ይምጣ ከአሜሪካ ወያኔ እንደሆነ ልዩነቶችን በንግግር ማስወገድ የማያዉቅበት ፀረ ህዝብ ስብስብ ነዉ። ወያኔ በዉይይት የሚያምንና ሠላም የሚገባዉ ቢሆን ኖሮ የደርግን ስርዐት ከደመሰሰ በኋላ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ የመጀመሪያዉን ህዝባዊ ሥርዐት መስርቶ በህዝብ እንደተወደደና በታሪክ እንደተወደሰ ይኖር ነበር።

ወያኔ ዉይይት የሚለዉ ህገ መንግስቱ በማያሻማ መልክ የሚፈቅደዉን መብት እንደገና ለማስፈቀድ ጎንበስ ቀና ማለትን ነዉ፤ሠላም የሚለዉ ደግሞ ዜጎች አፋቸዉን ዘግተዉና አንገታቸዉን ደፍተዉ ዘረኝትን አሜን ብለዉ ሲቀበሉ ነዉ። ወያኔ ሠላማዊ ትግል የሚለዉ አምስት እየቆየ የንግስና አመቱን ሲያከብርና ለሚቀጥለዉ አምስት ዐመት እራሱን ሲሾም የሚደረግለትን አጀብና የመልካም ምኞት መግለጫ ነዉ። ባጠቃላይ ለወያኔ በ"ሰላማዊ ትግልና" በ"ሠላማዊ ዉርደት" መካከል ምንም ልዩነት የለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ያንተን መልካም መስማት የማይፈልጉ ዘረኞች ምኒልክ ቤተ መንግስት ዉስጥ እየፈነጩ የሚሳሱልህና ዕድገትህን የሚሹ ልጆችህ ግን መኖሪያቸዉ እስር ቤት ወይም በስደት ከአገር ዉጭ ሆኗል። እንደ ህዝብ እንዳታስብ፤እንዳትሰበሰብና እንዳትወያይ በህግ ተከልክለሀል፤መሬት አልምተህ ለልጆችህ እንዳታወርስ የራሴ የምትለዉ መሬት የለህም።እንዲያዉ ለመሆኑ እስከመቼ ነዉ ወያኔ ጦምህን እያደርክ ምርት አድጓል እያለና ሳትበደር ዕዳ ከፋይ አድርጎህ በህልዉናህ እየዶለተ በስምህ እየነገደ የሚኖረዉ? አንተስ እስከመቼ ነው ያደኸየህንና ከሰዉ በታች ያደረገህን አስቀያሚ ስርዐት የምትሸከመዉ?

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የወያኔና የቅጥረኞቹ ንብረት በየደቂቃዉ እያደገ አንተ ግን ከደሳሳ ጎጆህ እየተፈናቀልክ፤ የወያኔ አባላት ገንዘብ የዉጭ ባንኮችን እያጣበበ አንተ ደም እያላበህ ለነገ ብለህ የቋጠርከዉ ገንዘብ ግን በዋጋ ግሸበት ሲተን፤የወያኔና የቅጥረኞቹ ልጆች ባንተ ገንዘብ አዉሮፓና አሜሪካ ዉስጥ ሲማሩ ያንተ ልጆች ግን የከብት ጭራ እየተከተሉ ሲኖሩ ዝም ብለህ የምትመለከተዉ እስከመቼ ድረስ ነዉ?

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ "የወጣትነት እድሜዬን ለህዝባዊ አላማ ሠዋሁ" ብሎ የሚመፃደቀዉ መሪ ተብዬዉ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን "ኢትዮጵያ" ብሎ በስሟ መጥራት የሚፀየፍ ሰዉ ነዉ። ይህንን ፀረ ህዝብ ግለሰብና እሱ የሚመራዉን የዘረኞች ስብስብ ከቆሰለዉ ጀርባህ ላይ በፍጥነት አሽቀንጥረህ ካልጣልክ የቆሰለዉ ጀርባህ እየጎበጠ የነፃነትህ አድማስ እየጨለመ በአጠቃላይ የእድገት ጎዳናህ እያጠረ ይሄዳል እንጂ እንደሰዉና እንደ ዜጋ ተከብረህ እፎይ ብለህ መኖር አትችልም። ነፃነት ሳይኖር ሰላም ሰላም ሳይኖር ደግሞ እድገት የለምና ነፃነት፤ ሰላምና እድገት የምትፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመንገዳገድ ላይ የሚገኘዉን የመለስ ዜናዊን ስርዐት ለመጣል ክንድህን አንሳ!

## ከአሜሪካ መንግሰት ጋር በየጊዜው በመላተም . . . ከገጽ 1 የዞረ

የግንቦት7 መሪ የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ለወያኔ አምባገነኖች ተላልፈው እንዲሰጡ ለአሜሪካ መንግስት ጥያቄ አቅርቦ የነበረው የመለስ ዜናዊው አሽከር በረከት ስመኦን፣ ከአሜሪካ መንግስት ያገኘው መልስ ተስፋ አስቆራጭ በመሆኑና እንዲያውም ዶ/ር ብርሀኑ ስራቸውን ያለምንም ችግር እንዲሰሩ መፈቀዱን በማወቁ በብስጭት የጻፈው ጽሁፍ እንደሆነ የሚናገሩት የውስጥ ምንጮች፣ ይህ የበረከት ጽሁፍ የወያኔ አቋም ተደርጎ እንደተወሰደም ለማወቅ ተችሏል።

ወያኔ በጸረ ሽብር ትግል ስም ከአሜሪካ መንግስት ለማግኘት አስቦ የነበረው ድጋፍ በውጭ አገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የግንቦት7 አመራሮች ባደረጉት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲሰናከል መደረጉን የሚናገሩት ምንጮች፣ የወያኔ ገዢዎችም በሁኔታው እጅግ እየተበሳጩ እንደሚገኙ የውስጥ ምንጮቻችን ተናግረዋል። ስለ ሁኔታው አስተያየታቸውን የሰጡን አንድ የግንቦት 7 የዲፕሎማሲ ክፍል አባል እንደተናገሩት ግንቦት 7 ከአሜሪካ መንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን ከአውሮፓ፣ ከአፍሪካና ከእስያ አገሮች ጋር ሳይቀር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እየመሰረተ ተቀባይነቱም ከእለት ወደ እለት ከፍ እያለነ ነው ብለዋል። በርካታ መንግስታት የወያኔን የዘረኝነት ፖሊሲ እየተረዱ በመምጣታቸው ቀስ በቀስ ራሳቸውን በማግለል ላይ ናቸው የሚሉት የግንቦት 7ቱ የዲፕሎማቲክ ክፍል አባል፣ አሁን ወያኔን በመደገፍ ላይ ያሉት መንግስታት ድጋፋቸውን እንዲያቋርጡ ለማድረግ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መሰራት እንዳለበትም ተናግረዋል።

ወያኔ ሰሞኑን በዩኤስ ኤ አይዲ ና በአሜሪካ ኢምባሲ ላይ ያቀረበው ክስ በእጅጉ ያስቆጣው የአሜሪካ መንግሰትም የወያኔ ባለስልጣናት በአስቸኳይ ማብራሪያ እንዲሰጡት ጥያቄ ማቅረቡን ለማወቅ ችለናል። የወያኔ ባለስልጣነት ግን እስካሁን ድረስ ኦፊሴላዊ ማብራሪያ አልሰጡም።

በወያኔና በአሜሪካ መንግሰት መካከል ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት እየተበላሸ የመጣው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ወደ ስልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን መረጃዎች አመልክተው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወያኔ ከአሜሪካ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ነገሮችን ሁሉ ሲያወግዝ መቆየቱን መረጃዎች ያሳያሉ።

የአሜሪካ የስቴት ዲፓርትመንት ያወጣውን ጠንካራ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሪፖርት ተከትሎ ፤ ወያኔ የዲፕሎማሲያዊ ቋንቋን ባልተከተለ ሁኔታ በአሜሪካ መንግሰት ላይ የስድብ ናዳ ማውረዱ የሚታወስ ሲሆን፣ እሱን ተከትሎም አንዳንድ በአሜሪካ የውጭ ተራድኦ ደርጅቶች ድጋፍ ይደረግላቸዋል የተባሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ዘግቶ እንደነበር ይታወሳል።

ይህም ሳያንስ ወያኔ ለነጻ አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ የተጓዙ የአሜሪካ ተማሪዎችን "የኦሮሞ ልጆችን ለምን ታስተምራላችሁ በሚል የዘረኝነት ስሜት" ተነሳስቶ ተጎሳቁለውና ክብራቸው ተዋርዶ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ አድርጓል።

ይህ የወያኔ እኩይ ድርጊት ሳይረሳ ደግሞ፣ በቀናት እድሜ ውሰጥ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ ስድብ አይጋ ፎረም በተባለ የወያኔ ድህረ ገጽ ላይ ቀርቦ ነበር። በዚህ ድህረ ገጽ ላይ የወጣው ጽሁፍ የፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማን አስተዳደር የባሪያ አስተዳደር ብሎ የሚሰድብ ሲሆን፣ በርካታ ኢትዮጵያውያንም በወያኔው ድህረገጽ ድርጊት በመበሳጨት ቁጣቸውን መግለጻቸው ይታወሳል። ችግሩ በዚህ ቀጥሎ ሰሞኑን ደግሞ ወያኔ የአሜሪካን መንግስት መንግስቴን ሊገለብጥ እያሴረ ነው የሚል ክስ ማሰማቱ፣ በወያኔና በአሜሪካ መንግስት መካከል የነበረው ትስስር እየላላና ምናልባትም ለመበጥስ እየተቃረበ ነው የሚሉ አስተያየቶች በመሰጠት ላይ ናቸው።

ወያኔ የአሜሪካን ባለስልጣናት ለመያዝ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ለተለያዩ የሎቢንግ ተቋማት ቢያወጣም የኦባማን ባለስልጣናት በመያዝ በኩል ውጤት እንዳላማጣለት መረጃዎች ያመለክታሉ። ወያኔን ደፋ ቀና ብሎ ሲያገለግል የነበረው ዶክተር ሳሙኤል አሰፋም፣ የስልጣን ጊዜውን ሳይጨርስ በሌላ ሰው እንዲተካ ለማድረግ ጥረት የተጀመረው፣ የአሜሪካ ባለስልጣናትን በብቃት ለመያዝ ባለመቻሉ ነው ተብሏል። ወያኔ ህዝብን በአደባባይ እያረደ ሳሙኤል አሰፋ ሊታደገው አይችልም የሚሉት ታዛቢዎች፣ የወያኔ የ18 አመት የማታለያ ዘዴ ሙሉ በሙሉ በመታወቁ ከእንግዲህ በዲፕሎማሲው መስክ ወያኔ የሚያስመዘግበው ድል አይኖርም ብለዋል።

በተያያዘ ዜናም ኢትዮጵያውያን በረዶና ጸሀይ ሳይበግራቸው በአሜሪካ ባለስልጣነት ቢሮ ፊትለፊት ሲያደርጓቸው የነበሩት ሰላማዊ ሰልፎች ውጤት በማምጣት ላይ መሆናቸውን አንዳንድ ሰዎች በመናገር ላይ ናቸው።

በቅርቡ የአሜሪካ መንግስት በወያኔ ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ ያስደሰታቸው ኢትዮጵያውያን እንደተናገሩት፣ "ወያኔ እስካሁንም ከአሜሪካ መንግስት በሚያገኘው ሁለንተናዊ ድጋፍ ነው በስልጣን ለመቆየት የቻለው፣ ከእንግዲህ ግን ሁኔታዎች ሁሉ እየተቀየሩ በመምጣታቸው የወያኔም እድሜ በዚያው ልክ እያጠረ ይመጣል" ሲሉ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በፈረንጆች አቆጣጠር መስከረም 13 ፤ 2009 በዋሽንግተን ከተማ የሚደረገው ታላቅ ሰልፍ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ይሳተፉበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ከአዘጋጆቹ የተገኘው መረጃ አመልክቷል። ሰልፉ የወያኔን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያጋልጥ ሲሆን በትልቅነቱም እስካሁን ከተደረጉት ሁሉ ሰልፎች ሊበልጥ እንደሚችል ይገመታል። ኢትዮጵያውአን በሰልፉ ላይ ተገኝተው የወያኔን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለአለም ህዝብ እንዲያሰውቁም አዘጋጆቹ ጥሪ አቅርበዋል።

## ቃሊቲ አሁን በርካታ ጠያቂዎች የሚጎበኟት ቦታ መሆኗ ተዘገበ

በየሣምንቱ ቅዳሜና እሁድ ከቃልቲ የማይጠፉ ጠያቂዎች ጀግኖች እስረኞችን መጠየቅ ለታሳሪዎቹ ብቻ ሳይሆን ለጠያቂዎቹም የመንፈስ እርካታ የሚሰጥ መሆኑ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ የዘወትር ጠያቂዎች ለአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ገለፁ። «እኔ ከቅንጅት ጊዜ ጀምሮ ቅዳሜና እሁድ እዚህ እንደተመላለስኩ ነው፤ እነሱ ማሰራቸውን ካላቆሙ እኔም መመላለሴን አላቆምም» ያሉት በግምት የ70 ዓመት እናት ናቸው። «ከቤተክስርቲያን መልስ እዚህ ደርሼ ‹እንዴት ከረማችሁ› ካላልኳቸውማ እግዜርም ቅር የሚሰኝብኝ ይመስለኛል» ያሉት ደግሞ የ65 ዓመት አዛውት ናቸው:: ወ/ት ብርቱካንና ከመፈንቀለ መንግሥት ሰበብ የታሰሩትን ጀግኖችን ለመጠየቅ ከሚመላለሱት ውስጥ አብዛኛዎቹ በእድሜ ወጣቶች መሆናቸው ዘጋቢያችን አረጋግጦልናል። ወጣቶች የሣምንቱ መጨረሻ ቀጠሮዎቻቸውን በቃሊቲ ማድረግ የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩበት ጊዜ ጀምሮ የተለመደ መሆኑን ዘጋቢያችን በላከው ሪፖርት አክሎ ገልፆልናል።

ከምርጫ 97 ወዲህ ቃሊቲ የሕዝብ ተወዳጅ ልጆች ማጎሪያ በመሆኑ እስረኞችን መጠየቅ ለብዙ ኢትዮጵያዊያን ከሣምንቱ ግዳጆቻቸው አንዱ አድርገው እንደሚወስዱት የሚታወቅ ሲሆን ወያኔ ደግሞ በጠያቂዎች ብዛት ስለሚቀና እስረኛ መጠየቅንም እንደሚከለክል ይታወቃል።

## ከሶማሊያ በአሳፋሪና አገርን ባዋረደ መልኩ በሽንፈት የተባረረው ወያኔ፣ በድጋሜ ሶማሊያን መውረሩ ተገለጸ

በሶማሊያ የሚገኙ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን እንደገለጹት የወያኔ ጦር ባለፈው አርብ ከሞቃዲሾ ወደ 300 ኪሜ ገደማ እርቃ የምትገኘውን በለደወይን የተባለችውን ቦታ ከእስላማዊ ታጣቂዎች እጅ በመውሰድ ተቆጣጥረዋታል።

የወያኔ ጦር ከእስላማዊ ሀይሎች በኩል ጠንካራ ፍልሚያ ሳይገጥመው ከተማዋን ለመቆጣጠር ቢችልም፣ ወደ ሶማሊያ ዘልቆ በገባ ቁጥር የሚጠብቀው የሞት ድግስ እንዳለ እስላማዊ ሀይሎች በመናገር ላይ ናቸው።

የወያኔ ጦር በአሜሪካና በሌሎች አገሮች ጦሩን ወደ ሶማሊያ እንዳይልክ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ የወያኔ ጦር ይህንን ማስጠንቀቂያ በመጣስ ወደ አካባቢው ለመዝመት የተገደደው የእስላማዊ ሃይሎች ጉልበት እየፈረጠመ ለወያኔ ህልውና ስጋት እየሆነ በመምጣቱ ነው የሚሉ አስተያየቶች በመደመጥ ላይ ናቸው።

የእስላማዊ ሀይሎችን አከርካሪ መትተን እንዳያንሰራሩ አድረገናቸዋል ብሎ ሲፎክር የነበረው መለስ ዜናዊ፣ ዘግየት ብሎ ደግሞ የውጭ መንግስታት ድጋፍ ካላደረጉልን ወደ ሶማሊያ አንገባም ብሎ መናገሩ የሚታወስ ሲሆን፣ የአሁኑ እርምጃው ከምን የመነጨ እንደሆነ በትክክል ለማወቅ አለመቻሉን ባለሙያዎች ይናገራሉ።

## አባ ጳውሎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ . . ከገጽ 1 የዞረ

አባ ጳውሎስ ለአለቃ አያሌው ታምሩ ጸሎት እንዳይደረግላቸው መከልከላቸውን ያስታወሱት አባቶቹ፣ ፓትሪያሪኩ ከወያኔ ሹማምንት ጋር በመሆን የሚሰሩትን የፖለቲካ ስራም አጋልጠዋል።

በተያያዘ ዜናም አገራቸውን ጥለው የሚጠፉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር መጨመር አስደንጋጭ እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። ባለፈው ሰሞን የአትሌቶች መጥፋት ዜና ሳይረሳ፣ ለልምድ ልውውጥ የተላኩ 4 ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችም እንዲሁ በእንግሊዝ አገር መጥፋታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

በኢትዮጵያ ወስጥ ያለው ዘረኛ አገዛዝ ፤ ህዝቡን ለርሀብ፣ ለበሽታና ለፖለቲካ ትርምስ በመዳረጉ እና ዜጎች በአገሪቻው የመኖር ተስፋቸው እየተመናመነ በመምጣቱ ለተለያዩ ጉዳዮች ወደ ውጪ የመውጣት ዕድል ያገኙ ሁሉ በየሄዱበት እንደሚቀሩ ታውቆአል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሥልጣን ላይ ያለውን ሥር'ዓት በታማኝነት ለማገልገል ከተሰለፉት ሰዎች መሃልም አንዳንዶች በአገዛዙ ፍጹም ዘረኛ አድልዎ'ኦ እየተማረሩ የስደትን ጎራ መቀላቀል መጀመራቸው የአደባባይ ምስጥር ሆኖአል::


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org